# ሀገርን እያፈረሱ ሀገሬ

*(ሊሊሳ ቱጆ- ከወንጂ) 10-21-16*

አሌፖ ከሶርያ ታላላቅ ከተሞች አንዷ ነች፡፡ የሀገሪቱ ዋና ከተማ ደማስቆም ከጥንታውያን ዋና ከተሞች ግንባር ቀደሟ ነች፡፡ ሁለቱም ከተሞች አሁን ሀገራችንን እንወዳለን ባሉ የዳኢሽ አማጽያን እንዳልነበሩ እየሆኑ ነው፡፡ አሌፖ ላይ አማጽያኑ እንቅስቃሴ ሲጀምሩ ክቡሩን የሰው ልጅ ሕይወት በመቅጠፍና ጥንታውያን ቅርሶችን በማውደም ነበር፡፡ አሁን ከተማዋም እንደ ከተማ ለመቀጠል እስከማትችልበት ደረጃ ደርሳለች፡፡

በአህጉራችን በአፍሪካ እየደረሱ ካሉ መሰል ውድመቶች የማሊውን ሳይጠቅሱ ማለፍ ምስክርነትን ጎዶሎ ያደርገዋል፡፡ በሀገሪቱ አማጽያን በወሰዱት አፍራሽ እርምጃ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ለሞት በሺዎች የሚቆጠሩት ደግሞ ለስደት ተዳርገዋል፡፡ ከዚህም ሌላ የሀገሪቱ ብቻ ሳይሆን የዓለም ቅርስ የሆነውና ጥንታዊ የቲንቡክቱ ሥልጣኔን የሚያሳዩ ቅርሶች እንዳልነበሩ ሆነው ወድመዋል፡፡ በሰሜናዊቷ ሀገር ሊቢያም በቀጠለ ፍጅት ትሪፖሊ፣ ቤንጋዚ፣ቱርቡክ እና ሲርት በተባሉ ታላላቅ ከተሞች ዘግናኝ ውድመት ደርሷል፡፡ የዚህች ሀገር አማጽያን ቆመንለታል ያሉትን ህዝብ ጭምር በአሰቃቂ ሁኔታ መግደላቸው የተለመደ ተግባር እየሆነ ነው፡፡ መቼም ቢሆን ሊቢያዊውን የሚፈጅ ለሊቢያዊ ቆሜአለሁ ብሎ መናገር አይችልም፡፡ የሶርያን  እና የሊቢያን አነሳን እንጂ በሌሎች ጥቂት ሀገራትም አማጽያን መሰል ውድመት እያደረሱ ነው፡፡

ወደ ሀገራችን ስንመጣም መስከረም 22 ቀን 2009ዓ.ም መከበር በነበረበት እና በሰላማዊነቱ በሚታወቀው የኢሬቻ በዓል ላይ በርካታ ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡ በሌሎች የሀገራችን ጥቂት አካባቢዎች በተለይም በኦሮሚያና አማራ ክልል አንዳንድ ከተሞች በተቀሰቀሱ አመጾች ሰዎች ለሞት እና ለእንግልት ተዳርገዋል፡፡ በባሕርዳር እና በጎንደር ብዙ ሺህ ሰዎች የሚተዳደሩባቸው ፋብሪካዎች እና እርሻዎች ወድመዋል፡፡ በአምቦ፣ በሰበታ እና በሌሎችም ከተሞች ከግለሰቦች እና አነስተኛ ነጋዴዎች ንብረት እስከ ትልልቅ ኢንቨስትመንቶች ወድመዋል፡፡

በሰበታ ከተማ ዙርያ ብቻ በደረሰ ውድመት 40 ሺህ ያህል ሠራተኞች ያስተዳድሩ የነበሩ ፋብሪካዎች ወድመዋል፡፡ በነባር ስኳር ፋብሪካዎችም በተለይም በወንጂ በርካታ ሔክታር የደረሰ ሸንኮራ አገዳ በአዋኪዎቹ ተቃጥሏል፡፡ የህብረተሰቡ ርብርብ ባይኖር የበለጠ

ውድመት ሊደርስ እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ በአርሲ ኔጌሌም ለ80 ሺህ ሰዎች አገልግሎት የሚሰጥ የውሃ ተቋም እንዳልነበር ሆኗል፡፡

በዚህ በኩል ልማት እየወደመ በሌላ በኩል ደግሞ “የኦሮሚያ ጊዜያዊ መንግሥት ተቋቁሟል” “አባይ መገደቡ ይቆማል፤ ግብጾች እንደፈለጋችሁ” እየተባለ ነው፡፡ ለሊቢያ የተጠቀሰው እዚህም ይሠራል፡፡ የኦሮሞን ሕዝብ እንዲሞት ምክንያት እየተኮነ ለኦሮሞ ህዝብ ቆሜአለሁ ማለት አይቻልም፡፡ ለአማራ ህዝብ ሞት ተጠያቂ እየተኮነም ለአማራ መቆም አይቻልም፡፡ ሕዝበ ሙስሊም እንዲሞት ምክንያት እየተኮነም ለሙስሊሙ መቆም አይቻልም፡፡ ለሕዝበ ክርስትያን ሞት ምክንያት  እየሆኑም ለክርስትያኑ ቆሜአለሁ ማለት አይቻልም፡፡

ለኦሮሞ ሕዝብ የቆመ አካል የኦሮሞን በዓል አብሮ ያከብራል እንጂ በበአሉ በፍጹም ለሞት ምክንያት አይሆንም፡፡ ለአማራውም ሕዝብ የቆመ ወገን በአማራው እልቂት ጮቤ አይረግጥም፡፡ ለኦሮሞ፣ ለአማራ፣ ለኮንሶ፣ ለወላይታ፣ ለክርስትያን፣ ለሙስሊም... የቆመ ድርጅት  ከጦርነት ነጋሪት ይልቅ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ወደ ሀገር ቤት ይልካል፡፡ ለህዝብ መቆም ከማውደም ኢንቨስት ማድረግ ነውና፡፡ ቢሮክራሲው እንኳ "አላሠራ" ካለ በሰላማዊ መንገድ ታግሎ ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡ ስለሚቻልም ነው እነ ማሕተመ ጋንዲ በሰላም ታግለው ለውጥ ያመጡት፡፡ በነገራችን ላይ መንግሥት ዘላለማዊ አይደለም፡፡ ሕዝብ ነው በዘላለማዊነት የሚቀጥለው፡፡

የተባለው ጊዜአዊ መንግሥት በኦሮሚያ ይመስረት እንኳ ቢባል የሚያስኬድ አይደለም፡፡ አብሮ የኖረን ሕዝብ ማበጣበጥ ነው የሚሆነው፡፡ ለመሆኑ 100% ኦሮሞ፣ 100% አማራ፣ 100% ትግራይ፣ 100% ጉሙዝ፣... አለ ወይ? አንድ ብሔረሰብ፣ ብሔር፣ ሕዝብ ራሴን ላስተዳድር ማለቱ መቼም ቢሆን መጣስ የሌለበት መብት መሆን አለበት፡፡ ያ ማለት ግን ከመሬት ተነስቼ ልገንጠል ማለት አይደለም፡፡

መበታተኗን በሚያልሙ እድገቷ የሚስቀናቸው  ወዳጅ ያልሆኑ ሀገራት ያሏት ሀገራችን የራሷ ዜጎች ጠላት ከሆኑባት በኦሮሞ ሕዝብ እንደሚነገረው ተረት እንደ ሦስቱ በሬዎች እና ጅብ መሆን ነው፡፡

ጥቁር፣ ቡራቡሬ እና ነጭ በሬዎች ለብቻቸው በጫካ ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ ከመዋደዳቸውም ሌላ አብረው ነበር የሚበሉት እንዲሁም ጠላታቸውን የሚከላከሉት፡፡ ይህ በመሆኑም ጅብ ሊያጠቃቸው አልቻለም፡፡ ስለዚህ ዘዴ ዘየደ፡፡ ቡራቡሬውን እና ጥቁሩን በሬዎች

ጠራቸውና “እናንተንኮ ጠላት የሚተናኮላችሁ ነጬን በሬ ከርቀት እያየ ነው ተለዩትና ለብቻችሁ አለስጋት ኑሩ” አላቸው፡፡

እነሱም ለጊዜው ባይቀበሉትም እየዋል እያደር “እውነት ሳይሆን አይቀርም” ብለው ከነጬ በሬ ተነጠሉ፡፡ በጉልበት ያላሸነፋቸው ጅብ በወሬ አሸነፋቸው፡፡ ነጬ በሬ በጅቡ ተበላ፡፡ ይኸው ጅብ አረሳስቶ ጥቁሩን በሬ "አንተን እኮ እንኳን ከርቀት ከቅርብም ለማየት ያስቸግራል፡፡ ሊያስበላህ የሚችለው ቡራቡሬው በሬ ስለሆነ ተለይተኸው ያለስጋት ለብቻህ ብትኖር ይሻላል" አለው፡፡

ጥቁሩ በሬም ነጬ በሬ በመነጠሉ ሳቢያ መበላቱን ሳያስታውስ "እውነት ሳይሆን አይቀርም" ብሎ ከቡራቡሬው በሬ ተለየው፡፡ በዚህ ጊዜ ሁለቱንም ለየብቻ ያገኛቸው ጅብ በቀላሉ በላቸው፡፡ ወገኖቼንም "አዉዉዉ" በማለት ጠርቶ አበላቸው፡፡

በመንግሥት ደረጃም ይሁን (ቢረጋገጥም ባይረጋገጥም) በግለሰብ ደረጃም ይሁን ግብጾች እየተከተሉ ያለው ከጅቡ ታክቲክ ተለይቶ አይታይም፡፡ እነሱ ለመተግበር እየፈለጉ ያሉት ቅኝ ገዢዎቻቸው በነበሩት እንግሊዞች የተጠቀሙበትን ከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ ነው፡፡ ለነገሩ እንግሊዞች ከፋፍለህ ግዛ እንዳላሉ ሁሉ በህዝበ ውሳኔ ከአውሮፓ ህብረት እንነጠል ባሉ ማግስት ምን ያህል ጸጸት ውስጥ እንደ ወደቁ ማየቱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡

እንደ ጅቡ ሁሉ ግብጾች ብቻቸውን አልበሉም፡፡ የፈለገ ተቃዋሚ ይሁን በውጭ ሀገር የሚኖር ግብጻዊ ብሔራዊ ጥቅምን አስመልክቶ ያለው አቋም ግን ከሞላ ጎደል አንድ ነው፡፡ ለአንድ ግብጻዊ አልሲሲ እና ግብጽ የተለያያዩ ሁለት ነገሮች ናቸው፡፡ ስለዚህ ሀገሪቱን የሚጎዳ ተግባር አይፈጽምም፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት ሆስኒ ሙባረክን ለመቃወም በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኀን የተጠራው የበርካታ ቀናት ሰልፍ ጎማ ከማቃጠል የዘለለለ ንብረት አልወደመበትም፡፡ በግብጽ መንግሥት እስከማስለወጥ የደረሰው ህዝባዊ ቁጣ የግብጽን ገዢ ፓርቲ እና የግብጽን መንግሥት የለየ ነበር፡፡ አማጽያኑ ሀገሬ የሚኗትን ግብጽን እና የወቅቱ መሪያቸውን ሆስኒ ሙባረክን ልዩነት ያገናዘቡ ነበር ከሞላ ጎደል፡፡

እዚህ በእኛ ሀገር ግን አመጹ መንግሥትን እና ሀገሪቱን በአንድ አውድማ የወቃ አፍራሽ ተግባር ይመስላል፡፡ የተጀመረው የአመጽ መንገድ በጊዜ መፍትሔ ካልተበጀለት እና መከላከል ካልተደረገ የዛሬ 40 ዓመት ገደማ የነበረውን አብዮት አስታዋሽ ነው፡፡ በወቅቱ ምንም ያህል እንኳ ንብረት ባይወድም የግል ቂም እስከ መወጣጫ ጸረ አብዮት፣ ደርግ፣ ቀይ ሽብር ፣ነጭ ሽብር፣ አናርኪስት፣ ፊውዳል ወዘተ ተብለው ሰዎች ተገድለዋል፡፡

እንደ ሰሞኑ አመጽ አይነት ማባባስ የግብጽ መንግሥት (ቢኖርበትም ባይኖርበትም) እና የግብጻውያን ሚና ዛሬ የተጀመረ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ኃያልነት እንቅልፍ የነሳቸው ግብጾች ኢትዮጵያ ላይ ማሴር የጀመሩት ጥንት ነው፡፡ በተለይ በዘመነ ክርስትና በሰላም ያልሞከሩትን በጦርነት፣ በጦርነት ያቃታቸውን በሸፍጥ ሞክረውታል፡፡ ለምሳሌ በፍትሐ ነገሥት "ከኢትዮጵያ ሰዎች ጳጳስ አይኑር" ብለው የቤተክርስትያን ሕግ እስከማውጣት ደርሰውም ነበር፡፡ ይህ የሆነው እስልምና ከመሰበኩ በፊት በመሆኑ ከእስልምና ጋር የሚያያዝበት አንዳችም ምክንያት የለውም፡፡ ባይሆን በክርስትና ሥም ግብጻውያን ራሳቸው ግብጻውያን ጳጳሳት ለኢትዮጵያ እየሾሙ ኢትዮጵያን በክርስትና ሥም ከመቆጣጠር ጋር ይገናኛል፡፡ ለዚህም ነው በአንድ የታሪክ አጋጣሚ ክርስትያን ያልሆነ ጳጳስ ለኢትዮጵያ "እስከመሾም" የደረሱት፡፡

በኢትዮጵያዊው ንጉስ በቀዳማዊ ዳዊት ጊዜ የኢትዮጵያን ፖለቲካ እንዳሻው ለመዘወር ካላቸው ቅዠት የተነሳ ጳጳስ አንልክም እስከማለት ደርሰዋል ግብጾቹ፡፡ የዋዛ ያልሆኑት አፄ ዳዊትም እኔም አባይን እዘጋለሁ በማለት “ጳጳሱን እልካሁ” ለማስባል አብቅተዋል፡፡

በእርግጥ አሁን እንደ አፄ ዳዊት ጊዜ አባይን እዘጋለሁ በማለት የግብጻውያንን ጉሮሮ ለማድረቅ የሚዘጋጅ ወይም የተዘጋጀ ኢትዮጵያዊ መሪ የለም፡፡ መሪው ብቻ ሳይሆን ግን ሁሉም የሀገሪቱን እድገት የሚመኝ ኢትዮጵያዊ አባይን ለፍትሐዊ ጥቅም ለማዋል ገንዘቡን፣ ጊዜውን እና ሕይወቱን በመስጠት አባይ ተገድቦ ተጋምሿል፡፡ ይህ በመሆኑ ግብጽ አትራብም፤ ሰሜን ሱዳን አታዛጋም፤ ኢትዮጵያ ግን ዘወትር በረሃብ ይነሳ የነበረ ህዝቧን ታበላለች፤ ታጠግባለች፡፡ አንዳችም ጥቅሟ እስካልተነካ ድረስ ግብጽ በዚህ አይኗ ደም የሚለብስበት ምክንያት የለም፡፡

ይሁን እንጂ ሰላማውያን ከመካከላቸው ቢኖሩም ይህንን ያልተረዱ ግብጻውያን  በሀገራችን ላይ ቢያሴሩ እና ያኮረፍን እኛን ይዘው ቢነሱ አያስገርምም፡፡

ለዚህም ነው በምርጫ ሥልጣን ያዙ የተባሉት የቀድሞ መሪ ያሁኑ እስረኛ መሀመድ ሙርሲ በኢትዮጵያ ላይ ዱላ ለመሰንዘር ሲመክሩ ያፈተለከ ቅሌታቸው ለሁላችንም በመገናኛ ብዙኀን ለጆሮአችን የበቃው፡፡ በአንድ የሥራ አጋጣሚ ከዓመታት በፊት እዚህ ያገኘሁት ግብጻዊ ዲፕሎማት በአብላጫ ሰበብ፣ በአናሳ ሰበብ ብሔረሰብን ከብሔረሰብ፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት ሊያጋጭ የሚችል ነገር በጥያቄ መልክ ሲቆሰቁስ የሰማሁት፡፡ ለምንድነው የእንትን ሃይማኖት ተከታዮች የብዛታቸውን ያህል ሥልጣን የሌላቸው

ብሎኛል በወቅቱ፡፡ ይሁንም እንጂ የተባለው ሃይማኖት ተከታዮች የሆኑ ከፍተኛ ባለሥልጣናት በወቅቱም ሆነ አሁን በክልል እና ወረዳ ደረጃም ሆነ በፌደራል መንግሥት ደረጃ አሉ፡፡

ሌላው ግብጻዊ ኢትዮጵያ ለሥራ በነበሩበት ወቅት ኢትዮጵያ ሁለተኛ ቤቴ ሲሉ ማድመጤ የቅርብ ጊዜ ትዝታዬ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እኚሁ ሰው ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ ወዳጃችን ባሏት ኢትዮጵያ ዙሪያ ከጎረቤት ሀገሮቻችን የጦር ሰፈር ለመከራየት ወጣ ገባ ማለታቸውን በጋዜጦች ላይ አንብቤያለሁ፡፡ የተሳካላቸው ግን አይመስልም፡፡ ወዳጃችን ባሏት ሀገር ዙሪያ የጦር ሰፈር መከራየትን ምን አመጣው?

እንደነዚህ አይነት ሰዎች ባኮረፍን በእኛ አፍ አሸዋ ለማላመጥ፣ በእኛ እጅ እባብ ለመጨበጥ ይሞክራሉ፡፡ የገዢው ፓርቲ አካሔድ ስላልተዋጠልን ብቻ ወይም መንግሥትን ስላተቀበልን ብቻ አሊያም እንዲህ ለምን አልሆነም በማለት ብቻ የሀገርን ጥቅም አሳልፈን ለመስጠት እንዳዳለን፡፡ የራሳችን የሆነውን ንብረት እናቃጥላለን፡፡ አባይ ቢገደብ ኃይል ያመነጫል፤ የደን ውድመትን ይቀንሳል፤ አፈር ተሸርሽሮ የተፋሰሱ ታችኛ ሀገሮች በደለል አይዋጡም፡፡

ቀደም ሲል እንደተባለውም ኢትዮጵያውያን ይጠግባሉ እንጂ ግብጻውያን አይራቡም አይጠሙም፡፡ ሱዳኖችም አያዛጉም፤ ከንፈራቸውም አይደርቅም፡፡ ሦስቱም ሀገራት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በእኛ አፍ አሸዋው የሚላመጥ ከሆነ ግን መዘዙ ብዙ ነው፡፡ እነሱን ለማስደሰት "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" ብለን "አይዟችሁ አባይ አይገደብም፤ የተገደበውም ይፈርሳል፤ እናንተ ብቻ እርዱን" የምንል ከሆነ ትርጉሙ ሀገር ማፍረስ ነው፡፡ ሀገር ወዳድ የሀገሩን ጥቅም አሳልፎ አይሠጥም፡፡ ሀገሬን የሚል "አባይ አይገደብም የተገደበውም ይፍረስ አይልም፡፡" ይህ ሀገርን ማፍረስ ነውና::

ለመሆኑ ሀገርን እያፈረሱ ሀገሬ ሀገሬ ማለት ከየት መጣ? ዛሬ ላይ በቁም ቅዠት ውስጥ ያሉ ሃይሎች "ሀገር እናፈርሳለን" ሲሉ እንሰማለን፡፡ ታሪክን ቢዘነጉት እንጂ፤ ለሀገራቸው አንድነትና ለሰንደቅ አላማቸው ክብር ሕይወታቸውን የገበሩ ቀደምት ጀግኖች አባቶቻችን ያቆዩአትን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሀገር ኢትዮጵያን ለማፈራረስ መመኘት ጉም እንደመጨበጥ ያህል ነው፡፡

ስለሆነም በጥፋት መንገድ የተሰለፋችሁ ከያዛችሁት እኩይ ተግባር የምትመለሱበት ጊዜ አሁን ነውና እጃችሁን ከመሰብሰቡ ውጪ ሌላ አማራጭ አይኖራችሁም፡፡ አማራጩ አንድና አንድ ብቻ ነው፤ የያዛችሁትን የጥፋት መንገድ ትታችሁ ካሻችሁ የሰላማዊ ትግል ሜዳውን መቀላቀል፡፡ አሊያ ሀገርን እያፈረሱ ሀገሬ ማለት አይቻልም! አያዛልቅምም!